# SAT እየተለወጠ ነው

## ማወቅ ያለባችሁ ይኸውና

የኮሌጅ ቦርድ PSAT እና SAT ፈተናዎቹን ከሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ስርእተትምህርት ጋር እና ለኮሌጅና ለስራ ዝግጁነት አስፈላጊዎቹ ክሂሎቶች ጋር ለማቀናጀት እንደገና ነድፎአቸዋል። የተከለሰው PSAT/NMSQT በኦክቶበር 2015 የሚጀመር ሲሆን SAT ደሞ በማርች 2016 ይጀመራል። ዳገመ-ንድፉ በፈተናው አወቃቀር፣ አስተዳደር፣ መተግበርያ ጊዜ፣ እና በማርክ አሰጣት ላይ ተፅእኖ ያደርጋል

### መልሶ የተነደፈው የSAT ገፅታዎች

- አንድ አማራጭ መጣጥፍ
- ከብዙ ምርጫ ጥያቄዎች/multiple choice ያነሱ ቁጥሮች
- ለተሳሳተ መልስ ቅጣት አለመኖር
- የ1600-ነጥብ መለኪያ

በሂሳዊ አስተሳሰብ፣ ፕሮብሌም አፈታት፣ እና የአሀዝ መረጃ ትንተና ላይ ተጨማሪ ትኩረት ይኖራል። ፈተናው ከCommon Core State Standards/የጋራ ዋነኛ የስቴት መመዘኛዎች ጋር ተቀናጅቷል።

ት/ቤቶች ለነዚህ ለውጦች የተዘጋጁ መሆናቸውን ለማረጋገጥ፣ MCPS ከኮሌጅ ቦርድ፣ ከርእሰመምህራን፣ ከት/ቤት ሰራተኞች፣ እና ከሌሎች ሽርኮች ጋር በቅርብ ተባብሮ ሰርቷል።

ምንም እንኳን SAT በአለም-አቀፍ ደረጃ እውቅና ያገኘ የኮሌጅ መግቢያ ፈተና ቢሆንም፣ ACT እና ACCUPLACERን ጨምሮ ተማሪዎች ሌሎች አማራጮችም አሏቸው። የትኛውን ፈተና መውሰድ እንዳለባቸው ለመወሰን ተማሪዎች ከት/ቤታቸው አማካሪ ጋር እንዲነጋገሩ ይደፋፈራሉ።

### ነፃ ግላዊ የSAT መለማመጃ

የኮሌጅ ቦርድ ከKhan Academy ጋር በመሻረክ ነፃ፣ ግላዊ የSAT መለማመጃ ለሁሉም ተማሪዎች ጀምሯል። ተማሪዎች በKhan Academy ድር ጣብያ ላይ ነፃ ሂሳብ መክፈት ይችላሉ እዚያም ወደሚከተሉት መዳረሻ ይኖራቸዋል—

- አራት የተሟሉ የልምምድ ፈተናዎች፣ እና በተጭማሪ የጥናትና የፈተና አወሳሰድ ምክሮች፤
- በሺዎች የሚቆጠሩ ጥያቄዎች፣ የቪዴዎ ትምህርቶች፣ እና ጥቆማዎች፤
- የልምምድ መስኮች ነጥሎ ለማሳየት የምርመራ ጥያቄዎች፤ እና
- የአሰልጣኞች አስተያየቶች።

በKhan Academy ምዝገባና በአዳዲሶቹ ፈተናዎች ተመሪዎችን ማገዝ ት/ቤቶች በፎል 2015 ይጀምራሉ።

ስለዳግመ-ንድፉ ተጨማሪ መረጃ፣ የKhan Academy/ካን አካዴሚ ሽርክና፣ እና ለተማሪዎችና ወላጆች መገልገያዎች ተጨማሪ መረጃዎች፣ **https://collegereadiness.collegeboard.org/satን** ይጎብኙ